# *<u>የፕሬስ መግለጫ</u>*

## ሃሳብን በነፃ የመግለጽ መብት ላይ የተቃጣ ጥቃት
## <u>ኢነጋማ የአባላቱን መብት ለማስከበር ወሰን አይገድበውም</u>

የፕሬስ ነፃነት በግለሰቦች ወይም በፖለቲካ ድርጅቶች መልካም ፈቃድ የሚገኝ ሳይሆን ሕዝብ መስዋዕት ከፍሎ የሚጐናፀፈውና የሚጠብቀውም የትግል ፍሬ ነው፡፡ ይህን ሐቅ የኢትዮጵያ ሕዝብና ከአብራኩ የተከፈሉት ልጆቹ በሚገባ ይገነዘቡታል፣ ለሠላምና ለዴሞክራሲ የቆሙ የሰው ልጆችም እንዲሁ፡፡

በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 29 ቁጥር 2 ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት፣ ሃሳቡን የመግለጽ ነፃነት እንዳለውና ይህንን ነፃነትም በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ-ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሃሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶች እንዳለው ተደንግጓል፡፡

ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸውንና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን አህጉራዊና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችና ኮንቬንሽኖች ተከትለውና የሕግ ጥበቃ ይደረግልናል በማለት የሕዝቡን ኢንፎርሜሽን የማግኘት መብት ለማስከበር የተቋቋሙ የነፃ ፕሬስ ጋዜጦችና መጽሔቶች ሃሳብና አመለካከቶችን በማንሸራሸርም ረገድ ላለፉት 14 ዓመታት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የነፃ ፕሬስ አባላት ጥረትና ሕጋዊ እንቅስቃሴ በገዥው ፓርቲና መንግሥት ዘንድ በበጐ ገጽታቸው ሳይታዩ ቆይተዋል፡፡

በተለይም የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር (ኢነጋማ) አባላት ለኅብረተሰቡ ኢንፎርሜሽን በማሰራጨታቸው ለእሥራት፣ ለወከባ፤ ለእንግልትና ለገንዘብ ቅጣት ከመዳረጋቸውም በላይ ከ50 በላይ አባላቱ ለስደት ተዳርገዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ በነፃ ፕሬስ አባላት ላይ የሚፈፀም ገደብ የለሽ ጥቃት ዛሬም ድረስ ያላባራ ሲሆን በአሳዛኝና በአሳፋሪ መልኩ ከሰሞኑ ደግሞ በስደት በሚኖሩባቸው ሃገሮች ጭምር እየተከታተሉ የማጥቃት ዘመቻ እየተካሄደባቸው ነው፡፡

የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነሐሴ 3 ቀን 1997 ይፋ ባደረገው መግለጫ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና ባለቤታቸው ወ/ሮ አዜብ መስፍንን ጨምሮ ከፍተኛ የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት «የስም ማጥፋት ወንጀል ተፈፅሞብናል» በማለት በውጭ አገር በስደት በሚገኙ 4 ኢትዮጵያውያን ላይ ክስ መመሥረታቸውን የገለፀ ሲሆን ተከሰሱ ከተባሉት መካከል የኢነጋማ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊና የፊያሜታ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበረው፤የኢነጋማ ዓለም አቀፍ ኮሚቴ አስተባባሪ ባልደረባችን ዳዊት ከበደ ይገኝበታል፡፡ ዳዊት ከበደ በስደት አሜሪካ ሊሄድ የቻለው መንግሥት «የፕሬስ ሕግ ተላልፈሃል» በሚል በመሠረተበት ሰባት ክሶች ምክንያት ለከፍተኛ አደጋና እስራት በመጋለጡ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ከሚመራበት ሕገ-መንግሥትና ግዴታ ከገባባቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች አግባብ ባፈነገጠ መልኩ፤ በስደት በሚኖሩ የኢነጋማ አባሎች ላይ በየትኛውም ወገንና ቡድን የሚካሄደውን ማንኛውንም ዓይነት የበቀል ርምጃ፣ ጥቃት፣ ወከባና በሕግ ሽፋን ክስ እየመሠረቱ የማንገላታትን ተግባር ማኅበሩ በጥብቅ ይቃወማል፡፡

ስለሆነም ኢነጋማ አባል የሆነባቸው ዓለም አቀፍ የፕሬስ ተቋማት (IFJ,IPI,IFEX,EAJA,AJU...) አቻ የሙያ ማኅበራት፣ የፕሬስና ሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች (CPJ,RSF,PEN,WAN,AI,HRW...) መላው ሰላም ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ በተለያዩ ሃገሮች ስደት ላይ በሚገኙ አባሎቻችን ላይ የሚቃጣውን ጥቃት በማወገዝ መንግሥትም ሆነ የገዥው ፓርቲ ባለሥልጣናት ከአፍራሽ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ድምፃቸውን ያሰሙ ዘንድ ኢነጋማ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማኅበር(ኢነጋማ)
የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
ነሐሴ 4 ቀን 1997
አዲስ አበባ

ክፍሌ ሙላት
ፕሬዚዳንት